# ጋዜጣዊ መግለጫ

የአሜሪካ ኤምባሲ፤
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
*2016/09*

ለተጨማሪ መረጃ ቀጥሎ በተመለከተው ቁጥር ይደውሉ፡-011-130-7033
ድረ-ገጽ፡- http://ethiopia.usembassy.gov

## የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ (USAID) በግብርና ንግድ ዘርፍ ያካሄደው እንቅስቃሴ ኢትዮጵያ በዘርፉ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንድትታወቅ አደረገ

*የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ በግብርና ምርት ገበያ ልማት ዘርፍ ባደረገው እንቅስቃሴ ያመጣውን ለውጥ ተሳታፊ ገበሬዎችና በግብርና ንግድ ግንባር ቀደም ሚና የተጫወቱ ግለሰቦች በተገኙበት ተወሳ*

**አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ፤የካቲት 8 ቀን 2008 ዓ.ም.፡-** የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ(USAID) በግብርና ንግድ ዘርፍ ሲያከናውናቸው የቆየውን የተለያዩ የግብርና ምርት ገበያ ልማት እንቅስቃሴዎች አማካኝነት የተገኙ ስኬቶችን ቀጣይነት ለማረጋገጥ ሲል በዛሬው ዕለት ለመንግሥት ኤጀንሲዎችና ለአጋሮች አስረከበ። በዝግጅቱ ላይ የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ዳይሬክተር ዴኒስ ዌለር ባደረጉት ንግግር፡- “ቀጣዮቹ አምስት ዓመታት ኢትዮጵያ በምግብ ራሷን ችላ የምናይበት ብቻ ሳይሆን፤ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን ምርቶች በማምረት ዓለምን እንደምታስደንቅ የምንጠብቅበት ነው” ብለዋል።

ከአምስት ዓመታት የትግበራ ሂደት በኋላ ከአንድ ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ አርሶ አደሮች ከመርሀ ግብሩ ተጠቃሚ የሆኑ ሲሆን፤ ወደ 6,000 የሚጠጉ የሙሉ ጊዜ የሥራ ዕድሎች በግብርናው ንግድ ዘርፍ ተፈጥረዋል።በሌላም በኩል በኢትዮጵያ በግብርናው ንግድ ዘርፍ በመርሀ ግብሩ በኩል የ27.5 ሚሊዮን ዶላር የመዋዕለ ንዋይ ፍሰት ተደርጓል።

ኤጀንሲው አርሶ አደሮች የሚጠቀሙባቸውን የግብርና ስልቶች ማሻሻል ይችሉ ዘንድ 260,000 ሄክታር በሚሆን መሬት ላይ የተለያዩ ሥልጠናዎች እንዲሰጣቸው አድርጓል። በሥልጠናውም ምክንያት የድኅረ መኸር የምርት ብክነት ቀንሷል። በዚህም ረገድ ኤጀንሲው በማሳ አቅራቢያ ለተካሄደ የቡና፣የሰሊጥ፣የበቆሎ፣የሽምብራ፣ የስንዴና የማር ሽያጭ ከ189 ሚሊዮን ዶላር በላይ የገንዘብ ድጋፍ አድርጓል።

ይህ የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ዋንኛ የግብርና ንግድ እንቅስቃሴ ከባንኮችና ከሌሎች የፋይናንስ ተቋማት ጋር በመተባበር የአርሶ አደሮች ምርት፣ክምችት፣ሽያጭና ትርፋማነት ለማሳደግ ይረዳ ዘንድ 137 ሚሊዮን ዶላር ለብድር እንዲውል ዕድሎችን አመቻችቷል። በጠንካራ መሠረት ላይ የቆመ ግብርናና የግብርና ማቀነባበሪያ ዘርፍ ፤ አርሶ አደሩ የተሻለ ገንዘብ ማግኘት የሚችልበትን ዕድል ይፈጥራል።

ፍላጎትና የገንዘብ አቅርቦትን ያጣጣመ የድጋፍ አሰጣጥን ተግባራዊ በማድረግ፤ የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ 400 ለሚሆኑ ድጋፍ ተቀባዮች ከ14 ሚሊዮን ዶላር በላይ የሰጠ ሲሆን፤ ድጋፍ የተደረገላቸው የአርሶ አደር ድርጅቶችና የግል ኩባንያዎች የተለያዩ አዳዲስ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ተጠቅመው የበለጠ ውጤታማና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ተደርጓል። ለፋብሪካ ማቀነባበሪያነት የሚያገለግሉ፣የመሞከሪያና የደረጃ መስጫ መሣሪያዎችን በማቅረብ

፣ዘመናዊ መጋዘንን በማደራጀት፣ምርታማነትን የሚያሳድጉ የተሻሻሉ ዝርያዎች በማቅረብ፣የድኅረ-መኸር ምርት ብክነትን በመቀነስ ዙሪያ ሥራዎች የተሠሩ ሲሆን፤160 ሚሊዮን የሚሆን የግብርና ምርት ወደ ውጭ ገበያ ተልኳል። ኤጀንሲው ባደረገው ድጋፍም በመቶዎች የሚቆጠሩ በግብርናው ንግድ ዘርፍ ግንባር ቀደም የሆኑ ግለሰቦችና ድርጅቶች በአራት አህጉራት በተካሄዱ ጉባኤዎችና የንግድ ትርኢቶች ላይ ተሳትፈው የኢትዮጵያን ምርቶች በዓለም አስተዋውቀዋል።

በመርሀ ግብሩ ከሚሠሩ የቴክኒክ ሥራዎች ባሻገር፤ ኤጀንሲው በዘርፉ የተሰማሩ አካላት የንግድ ክህሎቶችን በማሳደግ ላይ በማተኮር ለአርሶ አደሮች፣በዘርፉ የመሪነት ሚና በመጫወት ላይ ላሉ ሴቶች እና ለግሉ ዘርፍ አጋሮች በፋይናንስ አስተዳደር፣በንግድ ዕቅድ አነዳደፍና በአመራር ክህሎት ላይ ያተኮሩ ሥልጠናዎችን ሰጥቷል። በዚህ ማዕቀፍ ኤጀንሲው 2,000 የሚሆኑ የመጀመሪያ ደረጃ ዩኒየኖችን የሚወክሉ የ54 የገበሬ ማህበር የኅብረት ሥራ ማህበራትን አቅም አሳድጓል፤ለ1.9 ሚሊዮን አባላት በሥልጠናና እስትራቴጂያዊ የገንዘብ ድጋፍ ተደራሽ ሆኗል።

*በአሜሪካ አለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ የሚመራው የግብርና ምርት የገበያ አቅርቦት ማሳደጊያ ፕሮግራም በኢትዮጵያ የሚተገበረው መጪውን ትውልድ መመገብ (Feed the Future Initiative) የተሰኘ መርሀ ግብር ዋና አካል ሲሆን የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ለኢትዮጵያ መንግሥት የግብርና ዕድገት መርሀ ግብር ከሚያደርገው ድጋፍ ትልቁን ድርሻ የሚይዝ ነው። በዓለም አቀፍ ደረጃ ረሃብን ለማጥፋትና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በአሜሪካ መንግሥት የተመደበው 3.5 ቢሊዮን ዶላር፤የአሜሪካ መንግሥት የኢትዮጵያ ዋነኛ አጋር በመሆን የሀገሪቱ ኢኮኖሚ መሠረት የሆነውን የግብርናውን ዘርፍ ለማሳደግ ከፍተኛ እገዛ በማድረግ ላይ ይገኛል።*

###